**<u>በንግድና ቱሪዝም ቋሚ ኮሚቴ መጨረሻ ላይ በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት የተስተካከለ</u>**

## <u>አዋጅ ቁጥር ……/2017 የተስተካከለ</u>

## <u>የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ</u>

የነዳጅ ውጤቶች ካላቸዉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንጻር ስትራቴጂክ ምርቶች በመሆናቸዉ አቅርቦታቸው፣ ክምችታቸው፣ ስርጭታቸው፣ ደህንነታቸው፣ ጥራታቸው እና ዋጋቸው ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በጠበቀ እና በሰው ጤና፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ መከናወኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከአስመጪው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ተጠቃሚ ድረስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ፣ አስተማማኝ፣ ፍትሀዊ እና ተደራሽ የአቅርቦት፣ የስርጭት እና የችርቻሮ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሰንሰለት ውስጥ እየታዩ ያሉ ሕገ-ወጥ ተግዳሮቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዘርፉ የተሰማሩ የነዳጅ ተቋማትና ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ ልምድ በሚጠይቀው መሠረት በሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ደህንነቱ የተጠበቀና ሕጋዊ የነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሥርዓት ለማስፈን የላቀ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አዋጅ ቁጥር ---/2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ “የነዳጅ ውጤቶች” ማለት የተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅን፣ ፔትሮሊየም ጋዝን፣ ባዮ-ፊውልን ወይም ሲንተቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀናበር የተገኘ ንፁህ ወይም አግባብ ባለዉ መንገድ የተደባለቀ የነዳጅ ውጤት ሆኖ ቤንዚንን፣ ኬሮሲንን፣ ናፍጣን፣ ቀላልና ከባድ ጥቁር ናፍጣን፣ የአውሮፕላን ነዳጅ፣የተሽከርካሪ ቅባትና ዘይቶችን ያካትታል፤

2/ “ባዮፊዉል” ማለት ከተፈጥሮ ነገሮች በባዮሎጂካል ሂደት የሚገኝ የታዳሽ ኃይል ምንጭ ነዉ፣

3/ “መደባለቅ” ማለት የተሻለ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት የነዳጅ ውጤትን በህጋዊ መንገድ በተፈቀደለት ተቋምና በተቀመጠው የጥራት ደረጃ መሰረት ከባዮ-ፊውል ጋር የማቀላቀል ተግባር ነው፤

4/ “ባዕድ ነገርን መቀላቀል” ማለት አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሲባል በሕገወጥ መንገድ ዝቅተኛ ዋጋ ያለዉን ነዳጅ ከነዳጅ ውጤት ጋር ወይም የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ ሊያጓድሉ ከሚችሉ ከሌሎች ነገሮች ጋር መቀላቀል ነው፤

5/ “ማከማቸት” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን የጥራት ደረጃቸዉን ጠብቆ በቋሚ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ዴፖ ማቆየት ነው፤

6/ “ማጓጓዝ ” ማለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዘዴዎችን በመጠቀም የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኙ ማከማቻዎች ሀገር ውስጥ ወደሚገኙ ዴፖዎች ወይም ማደያዎች ወይም ለቀጥታ ተጠቃሚዎች የማድረስ ሂደት ነው፤

7/ “ግብይት ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከውጪ ሀገር ከመግዛትና ማስመጣት ጀምሮ እስከ ማደያ ንግድ ሥራ ድረስ ያለውን የእርስ በእርስ የንግድ ግንኙነት ያካትታል።

8/ “የግብይት ሰንሰለት” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከውጪ ሀገር ከመግዛትና ማስመጣት ጀምሮ እስከ ማደያ ችርቻሮ ንግድ ሥራ ድረስ የሚሰማሩ የግብይት ተዋናዮችን የእርስ በእርስ መስተጋብር የሚያካትት ትስስር ነው፤

9/ “የግብይት ተዋናይ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ለማስመጣት፣ ለማደባለቅ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወይም ተዛማጅ ተግባራትን ለማከናወን የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠዉ ሰው ነው፤

10/ “አስመጪ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከውጪ ሀገር ለማስመጣት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

11/ “አከፋፋይ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከአስመጪ ገዝቶ ለነዳጅ ማደያዎች ወይም ለቀጥታ ተጠቃሚዎች በጅምላ ለመሸጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

12/ “ነዳጅ ማደያ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከአከፋፋይ ገዝቶ ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በችርቻሮ ለመሸጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ነው፤

13/ “ቀጥታ ተጠቃሚ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከአከፋፋይ በጅምላ በመግዛት ለተፈቀደለት ፕሮጀክት ወይም የልማት ድርጅት ፍጆታ የሚያውል ሰዉ ነው፤

14/ “የመጨረሻ ተጠቃሚ” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን በችርቻሮ በመግዛት ለራሱ ፍጆታ የሚያውል ሰዉ ነው፤

15/ “ዲጂታል የክፍያ ስርዓት” ማለት የነዳጅ ውጤቶች ግዥ እና ሽያጭን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መፈፀም ነው፤

16/ “የፀና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት የግብይት ተዋናይ የነዳጅ ውጤቶችን ለንግድ ወይም ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት፣ ለመደባለቅ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወይም ተዛማጅ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን ሙያዊ ብቃት እንዳለው ለማረጋገጥ የሚሰጥ የፀና የጽሁፍ ማስረጃ ነው፤

17/ “የነዳጅ መሠረተ ልማት” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለመደባለቅ፣ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወይም ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውል መሠረተ ልማት ነው፤

18/ “ግንባታ ” ማለት የተያያዥ ህንጻዎችን ግንባታ ሳይጨምር የነዳጅ መሠረተ ልማት ግንባታ ነው፤

19/ “ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ” ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

20/ “ባለሥልጣን” ማለት የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለሥልጣን ነው፤

21/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

22/ “አግባብ ያለው አካል” ማለት በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል ንግድ ቢሮ ነው፤

23/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

24/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት እና በግብይት ተዋናዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡-

(ሀ) በነዳጅ ፍለጋና ልማት ዘርፍ በሚከናወኑ ሥራዎች፤ እና

(ለ) ለወታደራዊ አገልግሎት በሚውሉ የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>የግብይት ተዋናዮች ግዴታ</u>

## 4. <u>የአስመጪ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም አስመጪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ የሀገሪቱን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ዓመታዊ የነዳጅ ውጤቶች ግዥ ዕቅድ የማዘጋጀት፣ ከውጪ ሀገር የማስመጣት፣ የማከማቸት እና ለአከፋፋዮች የመሸጥ፤ በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ መሥፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመያዝ፤

2/ የሚያስመጣቸው የነዳጅ ውጤቶች ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ነዳጅ ነክ ስምምነቶች እና የሀገሪቱን የጥራት ደረጃ መስፈርቶች ያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

3/ ከመነሻ ወደብም ሆነ ከራሱ ዴፖዎች የነዳጅ ውጤቶችን ወደ ማጓጓዣ ለመጫን ጥያቄ ሲቀርብለት የሚጫነውን ነዳጅ ጥራት እና መጠን ትክክለኛነት አረጋግጦ ለአጓጓዡ የተሟላ የማጓጓዣ እና የጭነት ሰነድ የመስጠት፤

4/ ከመነሻ ወደብም ሆነ ከራሱ ዴፖዎች በየዕለቱ የሚጫኑትን የነዳጅ ውጤቶች አይነት፣ መጠን እና የተገዙበትን ዋጋ የሚያሳዩ ሙሉ መረጃዎችን የመያዝና ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤

5/ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መንግሥት  በወሰነው ዋጋ የመሸጥ፤

6/ ስላከናወናቸው ሥራዎች መረጃዎችን የመያዝ፣ የመተንተን እና በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሰራር ስርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤

7/ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ሀገሪቱ በመጠባበቂያነት ልትይዘው የሚገባውን የነዳጅ መጠን የማከማቸትና የማስተዳደር፤

8/ በመርከብ መዘግየትም ሆነ በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች የነዳጅ አቅርቦቱ ሲቀንስ ወይም ሲስተጓጎል ከመጠባበቂያ ክምችት እንዲወጣ የሚያስፈልገውን ነዳጅ መጠን ለባለስልጣኑ የማሳወቅ እና ሲፈቀድም የማሰራጨትና የወጣውንም ነዳጅ እንዲተካ የማድረግ፤

9/ በየአመቱ እያደገ የሚሄደውን የሃገሪቱን የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎት መሠረት በማድረግ የማከማቸትና የመጫን አቅሙን የማሳደግ፤

10/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር፡፡

## 5. <u>የአከፋፋይ  ግዴታዎች</u>

ማንኛውም አከፋፋይ  የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፦

1/ ጀማሪ ከሆነ በሥሩ ቢያንስ አምስት መቶ ሺ ሊትር የነዳጅ ውጤቶች በክምችት መያዝ የሚችል ዴፖ እና 4 ማደያዎችን ይዞ ሥራ የመጀመር እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመታት ውሥጥ ተጨማሪ 6 ማደያዎች የመገንባት፤

2/ ነባር ከሆነ በስሩ ቢያንስ አምስት መቶ ሺ ሊትር የነዳጅ ውጤቶች በክምችት መያዝ የሚችል ዴፖ እና 6 ማደያዎች ይዞ የመስራት እንዲሁም ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በተከታዮቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ ተጨማሪ 4 ማደያዎች የመገንባት፤

3/ የነዳጅ ውጤቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር ያለመቀላቀል እና ጥራቱን ሊያጓድል ከሚችል ማናቸውም ድርጊት የመቆጠብ፤

4/ ለነዳጅ ማደያዎች እና ለቀጥታ ተጠቃሚዎች የነዳጅ ውጤቶችን በጅምላ የማከፋፈል፤

5/ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መንግሥት በወሰነው ዋጋ የመሸጥ፤

6/ አጓጓዥ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች በተፈለገው መዳረሻ ማራገፉን የማረጋገጥ፤

7/ በሥሩ የሚሠራ ማንኛውም የነዳጅ ማደያ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በአግባቡ ማሠራጨቱን የመከታተል፤

8/ በማከማቻ ዴፖው የተራገፈውን፣ ያሠራጨውን እና በቀሪነት የሚገኘውን የነዳጅ ውጤቶች መጠን መረጃ በመያዝ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሰራር ስርዓት መሠረት በየወሩ መጨረሻ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤ እና

9/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር፡፡

## 6. <u>የነዳጅ ማደያ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የነዳጅ ማደያ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ለሚያቋቁመው ለእያንዳንዱ የነዳጅ ማደያ በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ መሥፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማግኘት፤

2/ የነዳጅ ውጤቶችን በችርቻሮ ለመሸጥ የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች የማስመርመር እና ሌሎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ቁሳቁሶችን አሟልቶ የመሥራት፤

3/ የሚመለከተው የመንግስት አካል በአግባቡ የሚሠሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የሰጠባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መቅጃ መሳሪያዎች ልኬት ሊያዛባ ከሚችል ማናቸውም ድርጊት የመቆጠብ፤

4/ የነዳጅ ውጤቶችን ውል ከገባው አከፋፋይ ብቻ በመግዛትና በመረከብ ነዳጅ ማደያው ውስጥ እንዲራገፍ የማድረግ እና ስለተራገፈው ነዳጅ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋው የቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት መሠረት ለአንግዡ፣ ለአከፋፋዩ እና ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል ተገቢውን መረጃ የመስጠት፤

5/ የነዳጅ ውጤቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር ያለመቀላቀል፣ ጥራቱን ሊያጓድል ከሚችል ማናቸውም ድርጊት የመቆጠብ እና ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በችርቻሮ የመሸጥ፤

6/ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መንግሥት በወሰነው ዋጋ የመሸጥ፤

7/ ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች ያልተቆራረጠ የሃያ አራት ሰዓት የሽያጭ አገልግሎት የመስጠት፤

8/ ነዳጅ በማደያ  ዉስጥ እያለ የሽያጭ አገልግሎት ያለማቋረጥ፤

9/ ከነዳጅ ውጤቶች ግብይት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ የመያዝና ሲጠየቅም ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የማቅረብ፤

10/ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ክፍያዉን በባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጠው የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት የመፈፀም፤

11/ ባለሥልጣኑ የሚዘረጋውን እና በህዝብ ማስታወቂያ የሚያሳውቀውን ዲጂታል የግብይት ሥርዓት ተግባራዊ የማድረግ፤ እና

12/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር፡፡

## 7. <u>የአንጓዥ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አንጓዥ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ማጓጓዣውን በሚመለከተው የመንግሥት አካል በየ6 ወሩ የማስመርመርና የጸና የካሊብሬሽን የምስክር ወረቀት የመያዝ፤

2/ ከነዳጅ ውጤቶች በስተቀር በማጓጓዣው ሌሎች ማናቸውንም ጭነቶች አለማጓጓዝ፤

3/ አስመጪው የሚሰጠውን የማጓጓዣና የጭነት ሰነዶች በመያዝ እንዲያጓጉዝ በተፈቀደለት የጉዞ መስመር ብቻ የማጓጓዝ፤ በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም ሰነዶቹን የማሳየት፤

4/ የጫነውን የነዳጅ ውጤት ከአከፋፋይ ጋር በገባው ውል መሠረት በተመደበለት መዳረሻ የማራገፍ እና የማስረከብ፤

5/ በማጓጓዝ ሂደት እንደውሉ ለመፈጸም የማያስችሉ ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት ሂደቱን የሚያስተጓጉሉ ሁኔታዎች ካጋጠሙት ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የማሳወቅ እና በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት የመፈጸም፤

6/ ከነዳጅ ማጓጓዝ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የመያዝና በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋው የቴክኖሎጂ የአሰራር ስርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል ሪፖርት የማቅረብ፤

7/ በነዳጅ ማጓጓዣው ጂ.ፒ.ኤስ የማስገጠም፤ እና

8/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን የማክበር፡

8. <u>የቀጥታ ተጠቃሚ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የቀጥታ ተጠቃሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ በደንብና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የቀጥታ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶችን በማሟላት ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ አቅርቦ ፈቃድ የማግኘት፤

2/ የተፈቀደለትን የነዳጅ ውጤቶች አይነት እና መጠን ከአከፋፋይ በመግዛት ለተፈቀደለት ፕሮጀክት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ዓላማ ብቻ የመጠቀም፤

3/ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች አጠቃቀም በተመለከተ መረጃ በመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤

4/ በማንኛውም ምክንያት የቀጥታ ተጠቃሚ መሆኑን ሲያቋርጥ ይህንኑ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት መሠረት በ15 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እና የነዳጅ ውጤቶችን ሲያስረክበው ለነበረው አከፋፋይ የማሳወቅ እና የተሰጠውን ፈቃድ ለባለሥልጣኑ የመመለስ፤

5/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ዝርዝር የአጠቃቀም ሁኔታዎችን የማክበር፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ተቆጣጣሪ አካላት፣ ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ግንባታ ፈቃድ

### 9. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የታችኛውን የነዳጅ ንዑስ ኢንዱስትሪ ልማት የሚያሳልጡ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ ፖሊሲዎችና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤በዘርፉ መንግሥትን ያማክራል፣

2/ የነዳጅ ግብይት እና አጠቃቀም ሥርዓትን በበላይነት ይመራል፤

3/ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዱ ረቂቅ መመሪያዎችን ያፀድቃል።

### 10. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ ተጠቃሚዎችን እና አካባቢውን ማዕከል በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት አዘጋጅቶ የነዳጅ ማደያዎችን ከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ ደረጃ በማለት ይመድባል፤ የተሰጣቸውን ደረጃ መሠረት በማድረግ የሚቋቋሙበትንና የሚሠሩበትን አካባቢ ከክልሎች ጋር በመሆን ይወስናል፤

2/ የግብይት ተዋናዮችን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በማዘጋጀትና መስፈርቱን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

3/ ማንኛውም አከፋፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ለሚገነባው ዴፖ እና የነዳጅ ማደያ ህጋዊ ፈቃድ ባለው አማካሪ የፕሮጀክት ጥናትና የድርጊት መርሐ-ግብር አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ በማድረግና ገምግሞ በማጽደቅ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፤ በመርሐ-ግብሩ መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፤

4/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ሲመረምር ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመመካከር በግብይት ሰንሰለት ውስጥ የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅና የአካባቢ ጥበቃን ለማረጋገጥ የሚረዱ የደህንነት ጥንቃቄ መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

5/ አማራጭ የግብይት አሠራሮችን ይዘረጋል፤

6/ የሀገሪቱን የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎት መጠን በማጥናት አመታዊ የነዳጅ አቅርቦት ጣሪያን ለነዳጅ አስመጪ ያሳውቃል፣ በፀደቀው ዕቅድ መሠረት የግዥ ሂደቱን ተከትሎ መገዛቱንና በመርሐ-ግብሩ መሠረት ወደ ወደብ ተርሚናል መግባቱን ይከታተላል፤

7/ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

8/ የግብይት ተዋናዮችን የውል ስምምነት ሰነድ እና የሪፖርት አቀራረብ ፎርማቶች ይመለከታል፣ አፈጻጸማቸውንም ይቆጣጠራል፤

9/ ከነዳጅ ውጤቶች ግብይት ጋር በተያያዘ ሕገ ወጥ ድርጊት በፈፀመ የግብይት ተዋናይ ላይ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሰረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

10/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚወጣ ደንብ በሚወሰን ተመን መሠረት የቁጥጥር እና የአገልግሎት ክፍያዎችን ያስከፍላል፤

11/ ለነዳጅ ውጤቶች ግብይት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 11. <u>አግባብ ያለው አካል ሥልጣንና ተግባር</u>

አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ አጓጓዡ ከአከፋፋይ ስለተረከበው የነዳጅ ውጤቶች መጠን እና ለተመደበላቸዉ ማደያዎች በአግባቡ ስለማራገፉ እንዲሁም ሌሎች ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

2/ የነዳጅ ውጤቶች በክልሉ ውስጥ በህጋዊ መንገድ ስለመጓጓዛቸው፣ ስለመሰራጨታቸው እና መንግሥት በወሰነው የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ መሠረት ስለመሸጣቸው ቁጥጥር ያደርጋል፤

3/ የነዳጅ ማደያዎች ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች በፍላጎታቸው እና በከፈሉት ዋጋ ልክ አገልግሎት መስጠታቸውን ያረጋግጣል፤

4/ ነዳጅ ማደያዎች በሌሉባቸው አካባቢዎች ነዳጅን በበርሜል ወይም በመሰል መያዣዎች መሸጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጥንቃቄ በመመርመር በጽሁፍ ፈቃድ ይሰጣል፤ ግብይቱ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ እና መመሪያ መሠረት መከናወኑን ይቆጣጠራል፤

5/ የነዳጅ ውጤቶች ከባዕድ ነገሮች ጋር ሳይቀላቀሉ ጥራታቸውን ጠብቀው ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች መቅረባቸውን ይቆጣጠራል፤ ጥራታቸው ተጓድሎ ሲገኝም በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤

6/ ተቆጣጣሪዎችን በመመደብ በክልሉ የሚካሄደውን የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ይቆጣጠራል፤

7/ በክልሉ የሚካሄደውን የነዳጅ ውጤቶች ግብይት መረጃ በማሰባሰብ፣ በመተንተን እናበማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

8/ የነዳጅ ውጤቶች ግብይትን በተመለከተ ከሚኒስቴሩ እና ከባለሥልጣኑ ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤

9/ በክልሉ ለሚካሄድ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

12. <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

1/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የጸና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በነዳጅ ውጤቶች ግብይት ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

2/ በነዳጅ ውጤቶች ግብይት መሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ቅድመሁኔታ በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት ።

3/ ማመልከቻ የሚቀርብበት፣ የሚገመገምበት፣ ተቀባይነት የሚያገኝበት እና የሚከለከልበት ሥርዓት እንዲሁም መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣ መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

4/ ባለሥልጣኑ የቀረበው ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)እና (3) መሠረት የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው ማመልከቻው በደረሰው በ30 (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የከለከለ ከሆነ ምክንያቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ መግለጽ አለበት፡፡

## 13. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት እና የሚታደሥበት ሁኔታ</u>

1/ ለማንኛውም የግብይት ተዋናይ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለ 3 ዓመት ፀንቶ የሚቆይ ይሆናል፣የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየ 3 ዓመቱ ማብቂያ 2 ወር ሲቀረዉ ጀምሮ መታደስ አለበት ፡፡

2/ ለእድሳት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ ይወሰናል ፡፡

## 14. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማስተላለፍ</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

## 15. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ</u>

1/ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ የአካባቢ ጥበቃን፣ የማህበረሰብ ደህንነትን፣ የአከፋፋይ አነስተኛ የነዳጅ ውጤቶች የማከማቸት አቅምንና በሥሩ የሚተዳደሩ የነዳጅ ማደያዎች ቁጥርን፣ የነዳጅ ውጤቶች ጥራት ደረጃን፣ የተዘረጋ የግብይት ሥርዓትን፣ ታክስ ማጭበርበርን ወይም ሌሎች ግዴታዎችን አስመልክቶ በዚህ አዋጅም ሆነ በሌላ ሕግ የወጡ ድንጋጌዎችን ተላልፎ ከተገኘ ጉድለቶቹን እስኪያስተካክል ድረስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የታገደበትን ምክንያት እና በ 3 ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ለግብይት ተዋናዩ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

3/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን አስተካክሎ እገዳው እንዲነሳለት ማመልከቻ ካቀረበ ባለሥልጣኑ እገዳዉን ያነሳል፡፡

4/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ካላስተካከለ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይሰርዘዋል፡፡

## 16. ስለግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ

1/ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የጸና የግንባታ ፈቃድ ሳይኖረው የነዳጅ መሠረተ ልማት ግንባታ ማካሄድ አይችልም፤ ሆኖም በአንድ ነባር የነዳጅ ተቋም ውስጥ ለሚካሄድ መደበኛ የጥገና ሥራዎች የግንባታ ፈቃድ ማውጣት አያስፈልግም፡፡

2/ የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ የግብይት ተዋናይ ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት የሚከተሉትን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የነዳጅ መሠረተ ልማት የፕሮጀክት ጥናትና የድርጊት መርሀ ግብር፤

ለ) አግባብ ባለው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያቤት ይሁንታ የተሰጠው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት፤

ሐ) የነዳጅ መሠረተ ልማቱ ማህበራዊ ፋይዳና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ጥናት፤

መ) የግንባታ ፕላንና ዝርዝር መሥፈርት፤

ሠ) የሚገነባው የነዳጅ ቧንቧ መሥመር ዝርጋታ ከሆነ መነሻውን እና መድረሻውን የሚያሳይ ፕላን እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የተሰጠ የቧንቧ መሥመሩ የሚያልፍበትን መሬት የመጠቀም ፈቃድ፤

ረ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተገለፁ ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች፡፡

3/ ባለሥልጣኑ የቀረበው ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው ማመልከቻው በደረሰው በ30 (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል ፣ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ የከለከለ ከሆነ ምክንያቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ መግለጽ አለበት፡፡

## 17. የግንባታ ፈቃድ የሚያበቃበት ጊዜ

1/ የነዳጅ ተቋም ግንባታ ፈቃድ በተሰጠ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ የተፈቀደዉ የግንባታ ሥራ ካልተጀመረ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

2/ የነዳጅ ተቋም ግንባታ ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ከ 6 ወር ዉስጥ ግንባታዉ ተጠናቆ ሥራ መጀመር አለበት፡፡

18. <u>የግንባታ ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ</u>

1/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ወይም በሰጠው የግንባታ ፈቃድ የተመለከቱት ግዴታዎች ወይም ገደቦች ያልተከበሩ መሆኑን ሲያረጋግጥ ፈቃዱን ማገድ ይችላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት እና ተገቢ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ለግብይት ተዋናዩ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

3/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን አስተካክሎ እገዳው እንዲነሳለት ማመልከቻ ካቀረበ ባለሥልጣኑ እገዳዉን ያነሳል፡፡

4/ የግብይት ተዋናዩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ካላስተካከለ ወይም ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ12 (አስራ ሁለት) ወራት ውስጥ የግንባታ ሥራውን ካልጀመረ ባለሥልጣኑ የሰጠውን የግንባታ ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

19. <u>ማደያ በሌለባቸዉ አካባቢዎች ስለሚፈጸም የነዳጅ ግብይት</u>

ማደያ በሌለባቸዉ አካባቢዎች የሚፈጸም የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይት ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ ይወሰናል፡፡

20. <u>ስለጠቋሚ</u>

ህገ-ወጥ የነዳጅ ውጤቶች ንግድ ወይም የኮንትሮባንድ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን ጠቁሞ ላስያዘ ሰው ጥቆማዉ ዉጤታማ ሲሆን የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፣ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 21. ስለአስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ ባለሥልጣኑ ይህንን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውንም የግብይት ተዋናይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የግንባታ ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ስለ መረጃዎች አያያዝ ወይም ስለ ሪፖርት ማቅረብ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ተላልፎ የተገኘ የግብይት ተዋናይ በመጀመሪያ ጥፋት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ በማስጠንቀቂያው መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ ካላደረገ ወይም በድጋሚ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈጸመ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ወይም የግንባታ ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

3/ ማንኛውም ነባር የግብይት ተዋናይ ይህ አዋጅ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ መስፈርቶችን አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላገኘ የንግድ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

4/ ማንኛውም አከፋፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 (1) ወይም (2) መሠረት የሚጠበቅበትን የነዳጅ ዴፖ እና ማደያዎች ካልገነባ የንግድ ፈቃዱ ይሠረዛል፡፡

5/ ከአከፋፋይ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች ከተሰጠው ፈቃድ ዓላማ ውጪ ሲጠቀም የተገኘ የቀጥታ ተጠቃሚ ፈቃዱ ይሰረዛል፤ ከአምስት ዓመት በፊት ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከት አይችልም፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ወይም የግንባታ ፈቃድን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቁ ዝርዝር መስፈርቶች በደንብ እና በመመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

## 22. ስለ ወንጀል ቅጣት

1/ የነዳጅ ውጤቶችን ከተፈቀደው ቦታ ውጪ ያከማቸ፣ ሊሸጥ ከሚገባው ሰው፣ ቦታ እና የግብይት ሥርአት ውጪ ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው የተያዘው የነዳጅ ውጤት ተወርሶ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ሁለት መቶ ሀምሳ ሺ እስከ አራት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ የነዳጅ ውጤቶችን ሆን ብሎ ከባዕድ ነገሮች ጋር በመቀላቀል ለግብይት ያቀረበ ማንኛውም ሰው ነዳጁ እንዲወገድ ተደርጎ ከአራት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር አንድ መቶ ሺ እስከ ሶስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የነዳጅ ውጤቶች መንግስት ከተመነው የመሸጫ ዋጋ በላይ ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው በመጀመሪያ ጥፋት ከብር ሁለት መቶ ሀምሳ ሺ እስከ ሶስት መቶ ሀምሳ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤ ድርጊቱን በተደጋጋሚ ከፈጸመ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4/ በሚመለከተው አካል የነዳጅ መቅጃ መሳሪያዎች የልኬት ሜትር ማስተካከያ ተደርጎበት በፕሎምፕ የታሰረውን የቆረጠ ወይም ልኬቱን ያዛባ ማንኛውም ሰው ከሦስት አመት እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

5/ የካሊብሬሽን የምስክር ወረቀት ሳይዝ ወይም ካልብሬት የተደረገውን የነዳጅ ውጤቶች ልኬት በማዛባት የነዳጅ ውጤቶችን ሲያጓጉዝ ወይም ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው የነዳጅ ውጤቶች ተወርሰው ከሦስት አመት እስከ ሰባት አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

6/ የተረከባቸውን የነዳጅ ውጤቶች ከተፈቀደለት የማጓጓዣ መስመር ውጪ ሲያጓጉዝ፣ ከተፈቀደለት ማራገፊያ ውጪ ሲያራግፍ ወይም ወደ ጎረቤት ሀገር በኮንትሮባንድ ሲያጓጉዝ የተገኘ ማንኛውም ሰው የተያዙት የነዳጅ ውጤቶች ተወርሰው ከአምስት አመት እስከ አስር አመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር አራት መቶ ሺ እስከ ሰባት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

7/ አግባብ ካለው አካል በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ የነዳጅ ውጤቶችን የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው አካባቢዎች ሲሸጥ የተገኘ ወይም በመመሪያ በተወሰነው መሠረት አደጋ ያስከትላሉ በተባሉ መያዣዎች ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው የተያዘው የነዳጅ ውጤት ተወርሶ እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ሶስት መቶ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

9/ የነዳጅ ግብይት የዲጂታል ሥርዓት ግዴታን የጣሰ፣ያጭበረበረ፣ተግባራዊ ያላደረገ የግብይት ተዋናይ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና እስከብር ሦስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

10/ የባለሥልጣኑን ወይም አግባብ ያለውን አካል የቁጥጥር ሂደት የተቃወመ፣ ያሰናከለ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ተፅኖ ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር ሁለት መቶ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

11/ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድርጊቶች የሕግ ሰውነት ባለው አካል የተፈጸሙ በሆነ ጊዜ ከብር ሰባት መቶ ሺ እስከ አንድ ሚሊዮን በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (4)፣ (5) ወይም (6) የተመለከቱትን ድርጊቶች ለሁለተኛ ጊዜ በመፈጸም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የግብይት ተዋናይ በዚህ አንቀጽ ከሚጣልበት ቅጣት በተጨማሪ ድርጅቱ ለአምስት ዓመት እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

13/ የባለሥልጣኑን የቁጥጥር ሥራ በህግ አግባብ እንዳይፈፀም ጉቦ በመቀበል ያሰናከለ ወይም የወንጀል ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር ሁለት መቶ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

14/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣል የወንጀል ቅጣት በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃን አያስቀርም፡፡

**23. <u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>**

*1/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት* በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በሚሸፈን ማናቸውም ጉዳይ ላይ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ በተሠጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በ10 (አስር) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደ ነገሩ አግባብነት ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ የባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ ቅሬታው በደረሰው በ15 (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3/ የባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ለሚኒስቴሩ የቅሬታ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ ሚኒስቴሩ በሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ ቅሬታ አቅራቢ ውሳኔው በተሰጠ በ60 (ስድሳ) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለፌደራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

24. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማስፈጸም ረገድ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

25. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ማንኛውም ነባር የግብይት ተዋናይ ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ6 (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

26. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

27. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1/ የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 838/2006 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

28. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣…….ቀን 2017 ዓ.ም**

**ታየ አጽቀ ስላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**